የቅዱሳን ህይወት መገለጫዎች

ስነፍጥረት በሙሉ በተለይም ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት የራሳቸው መገለጫዎች አላቸው::

ነፋስ የማይታይና የማይጨበጥ ቢሆንም መገለጫ አለው::

ጽድቅም እንዲሁ የራሱ መገለጫ አለው::

ኃጢያትም ምንም እንኳን ከሰው ተሰውረው ቢሰሩትም የራሱ መገለጫ አለው::

ዋና ዋና የቅድስና ሕይወት መገለጫዎች

- ፈቀደ ስጋንና ፍቅረ ዓለምን ቆርጦ መጣል
- በአካል፣በልብስ፣በጥላ ዳሶ ድውይ መፈወስ፣ሙት ማስነሳት
- በቃል ጠርቶ ድውይ መፈወስ፣ሙት ማስነሳት፣ጋኔን ማውጣት
- ባሕር ከፍሎ በደረቅ ማሻገር
- ፀሐይ ማቆም፣በረድ ማዝነብ
- ግንብ መናድ
- እሳት ማውረድና ጠላትን ማቃጠል
- በመንፈሳዊ ቅንዓት መቃጠል
- በሚታየው ሁሉ አለመደነቅ፣አለመደንገጥ/ሁል ጊዜ መጽናት/
- የተሰወረውን ሁሉ ማየት/መወቅ/
- የአገልግሎት ፍቅር መጨመር

- ሁሉን አንድ አድርጎ ማየት(አለማዳላት)
- ዝናብ እንዳደደዘንብ ማድረግና ማዝንብ
- ጥቂቱን የማበርከትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል

የቅዱሳን ማንነት

- በባህርዩ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር በረድኤት ያደረባቸውና በጸጋ የተዋሐዳቸው ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ናቸው::
  - በረድኤት ያደረባቸው
  - ፈቃደ ስጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው ያስገዙ
  - ከክህደትና ከጥርጥር ሕይወታቸውን ያራቁ
  - በተቀደሰ አኗ ኗር አግዚአብሔርን የመሰሉ
  - በምስጋና፣በገድል፣በትሩፋት ሕይወታቸውን የመሩ ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ::
- ቅዱሳን የምንላቸው

1. ቅዱሳን መላዕክት

- በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ የተፈጠሩ
- ለምስጋና ለተልእኮ የተፈጠሩ
- የእግዚአሔርን ቸርነት ወደ ሰው የሚያደርሱና የሰውን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርጉ
- ለምህረትም ለመዓትም የሚላኩ
- ቅዳሴና ማህሌት ምግባቸው የሆነ
- ከቅዱሳን ሰዎች ጋር አንድነት ያላቸው ፣‘‘እምኀበ አልቦ ሀበቦ፣ከነበው ነገር ሳይሆን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጥሯቸዋል’’

2. ቅዱሳን ሰዎች

ሀ. በህገ ልቦና

ቅዱሳን አበው

ከአዳም እስከ ሙሴ የነበሩት አባቶችና እናቶች ናቸው::ቅዱሳን የተባሉበት ምንም እንኳን መልካም ስራቸው ገነት መንግስተ ሰማያት ሊያስገባቸው ባይችልም

- የተቀደሰ መሰዋዕት ለእግዚአብሔር በማቅረባቸው
- ከአምልኮ ባእድ ይልቅ አምልኮተ እግዚዘዘብሔርን በመምረጣቸው
- ሕገ ጋብቻቸውንና ድንግልናቸውን በንጽህና በመጠበቃቸው
- የንስሀ ሕይወት ተጠቃሚ በመሆናቸው
- ፈቃደ ስጋን ለፈቃደ ነፍስ በማስገዛታቸው
- ከአመጸኞችና ከኃጢያተኞች ጋራ ባለመተባበራቸው/፪ ጴጥ ፪÷፭/
- ተስፋ ድህነትን ገንዘብ በማድረጋቸው

ለ. በህገ ኦሪት

ቅዱሳን ነቢያት

ነብያት የሚለው ስያሜ የተጸውኦ ስም ሳይሆን የግብር ስያሜያቸው ነው::ትንቢት ተናጋሪዎች ማለት ነውና ቅዱሳን ነቢያት ተብለዋል::

ቅዱሳን ያሰኟቸው ዓበይት ምክንያቶችም፡-

- ሀብተ ትንቢት ያላቸው /የተሰጣቸው/ መሆኑ
- አውነተኛው ትንቢት በራእ ወይም በሕልም ለእነሱ መገለጡ
- ሕዝባቸውን የመክሩና ይገስጹ ዘንድ ከእግዚአብሔር መላካቸው
- ወደፊት የሚሆነውን ሀሉ በእርግጠኛነት መናገራቸውና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።።

ሐ. በህገ ወንጌል

1. ቅዱሳን ሐዋርያት

በእግረ ስጋም በእግረ ጎሊናም ለትምህርተ ወንጌል ዓለምን ስለሚዞሩ ሐዋርያት ተብለው ተሰየሙ።።

እአነዚህም፡ መ

- ከዓለም የተጠሩና የተመረጡ / ወደ ዓለም የሚላኩ/
- የመንግስተ ሰማያት ሚስጥር የተገለጸላቸው
- አጋንንትን የማውጣት ስልጣን የተሰጣቸው
- የማሰርና የመፍታት / የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ የተረከቡ
- ምዕመናንን የመጠቅ ሐላፊነትየተጠለባቸው
- ዘላለማዊ ስልጣነ ክህነት የተሰጣቸው

2. ቅዱሳን ጻድቃን

ጻድቃን ማለት እውነተኞች ማለት ነው።። እነዚህም

- መላ ዘመናቸውን ከሰው ተለይተው ሆነ በማህበረሰቡ መካከል ሆነው ከጣዕመ ዓለም የተለዩ (ሉቃ ፳፫÷፮)

- በጾም በፀሎት ፣በስግደት፣በትህርምት፣በምናኔ ጸንተው የኖሩ
- ወደውና ፈቅደው ስለ ክርስቶስ ሁሉን እያጡ መከራን የተቀበሉ
- በምደረ በዳ፣በዋሻ፣በፍሩክታና በምድር ጉድጓድ መስቀሉን ተሸክመው የዞሩ(የኖሩ)
- ወደናቁት ዓለም ዳግም ላለመመለስ የወሰኑ
- አገራቸውን፣ህዝባቸውን ና ቤተክርስቲያናቸውን በጸሎት ለመጠበቅ የሚተጉ
- ሰማያዊ አገራቸውን በመናፈቅ፣ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅና ፈጣሪያቸውን በመስደሰት ምድራዊ አኗኗራቸውን የፈጸሙና የመሳሰለውን ተጋድሎ የደረጉ ቅዱሳን ጻድቃን ተብለው ይጠራሉ::

‹‹ጽድቅን የሚሰራ ሁሉ ጻዲቅ ነው::›› ተብሎ ተጽፎአልና (፩ኛ ዮሐ ፫÷፯)

3. ቅዱሳን ሰማዕታት

ሰማዕታት ማለት ‹‹ የእውነት ምስክሮች ››ማለት ነው::

እነዚህም:-

- በክርስቶስ የባህሪ ዐምላክነት ያመኑ
- እውነት ለመመስከር የጸኑ፣ የተጉ
- በዓላውያን ነገስታትና በመናፍቃን ፊት ሳሰሰፍሩና ሳይፈሩ የክርስቶስን የባህሪ አምላክነት የመሰከሩና ከእነሱም ልዩ ልዩ ጽወትወ መከራ የተቀበሉ ናቸው::

ፀ ቆሮ ፲፩÷፳፫-፳፯

4. ቅዱሳን ነገስታት

በህዝብ ላይ አግዚአብሔርጋስታት የሾማቸው ሰዎች የሚጠሩበት ነው::ነገስታት የተለዩ የተመረጡና የተቀቡ ሆነው ሀገርንና ህዝብን የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ናቸው::ራሳቸውን ለእግዚያብሔር አደራ ሰጥተው የቅድስና ሕይወትን የሚመሩትና ቅዱስ የሚለው ስም የሚቀጸልላቸው ደግሞ የሚከተሉትን ነጥቦች አሟልተው ሲገኙ ነው::

- እንደ አህዛብ ነገስታት በስልጣነቸውና በሀብታቸው የማይመኩ ሆነው ሲገኙ
- ሀይማኖትን ከምግባር ጋር አዋህደው(አጣምረው)ሲይዙ
- ሕይወታቸውን ለእገዚአብሔር አሳልፈው ሲሰጡ
- ለሚመሩት ህዝብ እውነተኛውን ፍትህ ርትዕ ሲሰጡ
- በሚያስተዳድሩት ሕዝብ መካከል አድልኦ እነዳይፈጸም ሲጠነቀቁ
- ከህዝባቸው የሚቀርብላቸው ገጸ በረከት ስራቸውን እንዳያዛባባቸው ሲያደርጉ
- አንድአንዶችም የመጨረሻ ህይወታቸውን በምናኔ የፈጸሙ ሆነው ሲገኙ ቅዱሳነ ነገስት ተብለው ይጠራሉ ለምሣሌ፡- ነብይ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት አብርሃ ወአጽብሃ፣ ንጉስ ካሌብ ፣ንጉስ ላሊበላ ፣ይምርሐነ ክርስቶስና የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል::

5.ቅዱሳን ሊቃውንት

ሊቃውንት የሚለው ሥያሜ የእውቀት(የማዕረግ) ሆኖ ቅዱሳን የሚለውን ማዕረግ ማግኘት የቻሉት ሊቃውንቱ፡-

- በእግዚአብሔር ገላጭነትቅድሳት መጻህፍትን የጻፉ (የተረጎሙ)
- መናፍቃንን በእውነተኛ ትምህርታቸው የገሰጹና ያሳፈሩ
- አሰረ ፍኖታቸውን የሚከተሉ ደቀመዛሙርትን ያፈሩ
- ስለ ሐይማኖታቸው እንደ ሰማዕታት መከራን የተቀበሉ....ወዘተ በመሆናቸው ነው፡፡

ለምሣሌ፡- ቅዱስ አትናቴዎስ፣ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ቅዱስ ቄርሎስ፣ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፣ቅዱስ ያሬድ፣አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

6. ቅዱሳን ጳጳሳት

ጳጳሳት የሚለው ስያሜ ከቤ/ክ የክህነት ደረጃዎች መ ካከል አንዱ ሲሆን በድንግልና ህይወት፣በመንፈሳዊ ትምህርትና አገልግሎት ለተጉና ለተመረጡ አባቶች የሚሰጥ ነው፡፡

ቅዱሳን የሚያሰኛውም፡-

- በተሰጣቸው መንፈሳዊና ሰማያዊ ስልጣን በአግባቡ የሰሩበት
- የድንግልና ሕይወታቸው ንና ስልጣናቸውን በንጽጎና የጠበቁ
- መንጋውን በመጠበቅና በማሰማራት የተጉና ስለ መንጋው ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ
- በትምህርታቸውና በጸሎታቸው ቤ/ክርስቲያንን የጠበቁ
- ከመናፍቃን፣ከዓላውያን ነገስታትን ከእኩያት ፍትወታት ከኃጣውእ መላ ዘመናቸውን እየታገሉ መከራን የተቀበሉ.....ወዘተ በመሆናቸው ነው፡፡

7 ቅዱሳን መነኮሳት

መነኮሳት የሚለው ሥያሜ ከዓለማዊ አስተሳሰብ ና ምኞት የራቁ ወደውና ፈቅደው ተድላ ዓለምን የናቁና የተው አባቶችንና እናቶችን ሕይወት የሚመለከት ነው ::

አጀማመሩም በ 3 ኛው መቶ ክ/ዘመን በ ግብፅ በረሃወች በገዳመ አስቂጥስ ነው ::የድንግልና ህይወትን በቆብ መለየት የተጀመረውም በግብፅ አባቶች ነው::

- መነኮሳት ቅዱሳን የሚለውን የክብር መዓረግ የሚያገኙት...

❖ጀምረው እስኪጨርሱ ከዓለማዊ አኗኗር አስተሳሰብና አመለካከት ከራቁ

❖ለመንግስተ ሰማያት ሲሉ ራሳቸውን ጃንደረባ ካዳረጉ

❖የዓለምን ነገር ትተው መንፈሳዊውን ነገር ብቻ የሚያስቡና የሚፈጽሙ ከሆኑ

❖እንስሳዊ ግብርን ድል ከነሱና ጸብአ አጋንንትን፡ ድምፀ አራዊትን ፡ግርማ ሌሊትን ታግሰው ከታገሉና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት ጸንተው ከተጋደሉ ነው፡፡

- በዚህ ዓይነት ህይወት ጸንተው ካሸነፉና ከተጠቀሙ አባቶች መካከል አባ እንጦስ ፡አባ መቃርስ ፡አባ ጳኩሚስ ፡አባ ኪሮስ፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፡አቡነ አረጋዊ ፡አቡነ ተ/ሀይማኖት ፡አቡነ እየሱስ ሞዓ እና የመሳሰሉት ን መጥቀስ ይቻላል፡፡

8 ቅዱሳት አንስት

አንስት የተጸውኦ ሥያሜ ነው፡፡ከዘመነ አበው እስከ እለተ ምጽአት የተነሱና የሚነሱ እናቶቻችንና ልጆቻችን ቅዱሳት የሚለውን የከብር ማዕረግ የተቀበሉት ና የሚቀበሉት በኖሩት ና በሚኖሩት የቅድስና ህይወት ሲሆን

ለመጥቀስ ያህልም አንስትን ቅዱሳት ያሰኛቸው፡

- ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው በመስጠታቸው፤
- እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ በማድረጋቸው ፤
- በተሰ ቀለበት ዕለትም ከመስቀሉ ስር ባለየታቸው፤
- የትንሳኤው ምስክሮች በመሆናቸው
- መላ ዘመናቸውን በእግዚአብሔር ቤት በመኖራቸው፤(ሉቃ፪ ÷ ፴፯
- ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት የድርሻቸውን በማበርከታቸው፣
- በተሰጣቸው ጸጋ ፀንተው ፈጣሪአቸውን በማገልገላቸው፣
- የንጽሕናና የቅድስና ሕይወት ወደውና አጽንተው በመያዛቸው፣